# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ሐብታሙና ድሀው ሰው



ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: M. Maillot; Lazarus
የተተረጎመው: Abel Eshetu
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Maillot; Sarah S.

ታሪክ 44 ከ 60 ዎቹ መሃከል

**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

አማርኛ

Amharic

ብዙዎቹ የሐይማኖት መሪዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘብን እንደሚወዱ ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ሐብት ያለ እግዚአብሔር ዋጋ ቢስ እንደሆነ ይነግራቸው ነበር።



1

የሁለት ሰዎችንም ታሪክ ነገራቸው። ሐብት የዘላለምን ሕይወት ሊገዛ አይችልም።



2


በውድ ዋጋ የተገዙ በርካታ
ልብሶች የነበሩት አንድ
ሐብታም ሰው ነበር።
3


ሐብታሙ ሰው ውድ ውድ ምግብ ይመገብ ነበር። በርካታ አይነት
ምግብ ይቀርብለታል። ቁርስ፣ ምሳና እራቱ እጅግ ያማረ ምግብ
ነበር። ገንዘቡን ምርጥ ለሆነ ምግብ ያውለው ነበር።
4


በሐብታሙ ሰውዬ ደጃፍ ላይ ግን አንድ በጣም ድሀ የሆነ
የተራበና የሚለምን ነው ተኝቶ ነበር። ስሙ አልዓዛር ይባላል።
5


ድሀው አልዓዛር ቁስል ነበረበት።
በሽታ ሳይዘው አልቀረም። ክፉ
ሰዎች አቁስለውት ይሆናል።
ወይንም ድሀ በመሆኑ
የተመጣጠነ ምግብ ስለማያገኝ
ሰውነቱ ቆስሎ ሊሆን ይችላል።
6


አልዓዛር
ምግብ
ይፈልጋል።
የሀብታሙ
ሰውዬን
ትርፍራፊ
ምግብ
ለመብላት
የሚፈልግ
ይመስላል።
7


በርካታ
የመንደር
ውሾች ምግብ
ሊለቃቅሙ
በአጠገቡ
ይመጡ ነበር።
ውሾቹም
ቍስሎቹን
ይልሱ ነበር።
ማንም
ስለአልዓዛር
ግድየለውም
ነበር።
8



አንድ ጠዋት ግን አልዓዛር ከእንቅልፉ አልነቃም ነበር። ድሀው፣ ወዳጅ የሌለው እና የተራበው አልዓዛር ሞቶ ነበር።
9




አልዓዛር እንደሞተ ወዲያው ታላቅ ደስታ ሆነለት። መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት ብሎ ኢየሱስ ተናገረ። እግዚአብሔር አልዓዛርን አጽናናው።
10




ሐብታሙ ሰውም ሞተ። ሐብትና ገንዘቡ ሊያድነው አልቻለም። ሞትን ሊከለክልለት የሚችል አልነበረም።
11




ሐብታሙ ሰው ተቀበረ። ምናልባትም ትልቅ ስነስርዓት ተደርጎለት ይሆናል። ሰዎች ሐብቱንና ስኬቱን በማድነቅ አውርተው ይሆናል። ግን ይህ ሁሉ ምንም አልጠቀመውም። ነፍሱ ወደ ሲኦል ገብታለች።
12




እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።
13




አብርሃም ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ ሁሉ ነገር ነበረህ አልዓዛር ግን ምንም አልነበረውም። ሕይወቱ የከፋ ነበር፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሰቃያለህ።
14

ከዚህ ወደ እናንተ
ሊያልፉ የሚፈልጉ
እንዳይችሉ፥ ወዲያ
ያሉ ደግሞ ወደ እኛ
እንዳይሻገሩ በእኛና
በእናንተ መካከል ታላቅ
ገደል ተደርጎአል አለ።



15

አምስት ወንድሞች አሉኝ፤ አልዓዛርን
ላከውና ወደዚህ ስቃይ ስፍራ
እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።



16

አብርሃም ግን፡- መጽሐፍ ቅዱስ አለላቸው፤
እርሱን ይስሙ አለው። መጽሐፍ ቅዱስን
የማያምኑ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ
ቢነሣ አያምኑም አለው።



17

ኢየሱስም የሐብታሙንና ድሀውን ታሪክ በጨረሰ
ጊዜ የሐይማኖት መሪዎቹ ራሳቸውን እንዲህ
ብለው ሳይጠይቁ አይቀርም። *"ከእግዚአብሔር
ይልቅ ሐብትን እወዳለሁ?"* የእግዚአብሔርን
ቃል የማያምኑ ከሆነ ምን ሊገጥማቸው
እንደሚችል አውቀዋል።



18

ሐብታሙና ድሀው ሰው

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ሉቃስ ወንጌል ምዕ. 16

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16